# የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር ኢንተርንሽፕ ረቂቅ መመሪያ

## አጭር ማብራርያ (ሐተታ ዘምክንያት)

## 1. መግቢያ

የተሻሻለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የተግባር ስልጠና (ኢንተርንሽፕ) በሁሉም የትምህርት መስኮች የስርአተ ትምህርት አካል እንዲሆንና ሃያ ከመቶ ያላነሰ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች በሁሉም የስልጠና መስኮች ሰባ ከመቶ ያላነሰ በኢንዱስትሪ የተግባር ልምምድ ወይም ስልጠና እንዲሆን የደነገገ ቢሆንም አተገባበሩ ላይ ክፍተት መኖሩን ይስተዋላል። ከክፍተቶቹ መካከል ኢንዱስትሪው በኢንተርንሺፕ ዙሪያ ባለው የግንዛቤ እጥረት፣ የዝግጁነት ውስንነት እና ኢንተርኖች የሚጠበቅባቸውን ክህሎት እንዲያሟሉ በተገቢው የኢንዱስትሪ ስራ ክፍል ስለማያሰማራቸው እየጨመረ የመጣውን ኢንተርንሽፕ ፍላጎት፣ ጥራት እና ተደራሽነት ለማስተናገድ ተግዳሮት ሆኗል።

በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንደስትሪዎች መካከል የተማሪዎች እና የሰልጣኞች የተግባር ልምምድ ትግበራን ለማሻሻል በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ ማጠናከር አንዱ መፍትሄ ነው።

በተጨማሪም የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የሰው ኃይል የማፍራት ስራ ላይ ቅንጅታዊ የኢንተርንሽፕ ተሳትፎ፤ መንግስት ያለመውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል እና ማስጠበቅ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል የማፍራትን ሂደት በህግ ማዕቀፍ መደንገግ ያስፈልጋል።

በመሆኑም በዚህ ረቂቅ መመሪያ የኢንተርንሽፕን ተግዳሮት የሚፈታ እና በትስስር አዋጅ 1298/2015 የተደነገጉ ጉዳዮችን በዝርዝር ለማስቀመጥ ተገቢ የምደባ መስፈርት፣ የክትትል እና ግምገማ እንዲሁም ውጤታማ የተግባር ላይ ልምምድ ስርዓት በስራ ላይ ለማዋል ተዘጋጅቷል።

## 2. አላማ

የዚህ ረቂቅ መመሪያ ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትዎች መካከል የተግባር ልምምድ አግባብነት፣ ተደራሽነትንና ጥራትን ማሻሻል ነው። ስርዓት ለመዘርጋት እና የትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 ተከትሎ የማስፈጸሚያ ስርዓት ለማዘጋጀት ነው።

## 2. የባለድርሻ አካላት ድርሻ

የረቂቅ መመሪያው የዝግጅት ሂደት ላይ ከሁሉም የትስስር አካላት የባለሙያ ስብጥር ተዋቅሮ የተሰራ ሲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድረግ እና አስተያየት መቀበል ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ ሁሉም የግልና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የተመረጡ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች እና ምርምር ተቋማት እንዲሁም የተመረጡ የቴክኖሎጂና ሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ተቋማት ተሳትፈውበት ግብአት ተገኝቷል። በተጨማሪም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በተለያየ መድረክ መመሪያው ቀርቦ ተተችቷል ግብአት እና የማስተካካያ ሀሳቦች ተወስደው ማስተካካያ ተደርጓል። የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በኢንተርንሽፕ ላይ የተሰጡትን የማስተካከያ ሃሳቦች እና እያንዳንዱ እርማት ከዚህ ሰነድ በአባሪ ተያይዟል።

## 4. የመመሪያው ይዘት

መመሪያው በአስራ ስምንት አንቀጾች የተዋቀረ ነው። የዚህ መመሪያ የተፈጻሚነት ወሰን በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ 1298/2015 በተጠቀሱ የትስስር አካላት ላይ ነው።

የመመሪያው ክፍል ሁለት ስለኢንተርንሺፕ ልምምድ አይነት እና የቆይታ ጊዜ የሚደነግግ ነው። የኢንተርንሽፕ አተገባበር በተለያዩ ተቋማትና የትምህርት መስኮች የተለያየ ስያሜና አተገባባር ያለው በመሆኑ በአዲስ መልክ ተለኪና ተለኪ ያልሆነ ኢንተርንሽፕ ተብሎ በሁለት በመክፈል በዝርዝር እንዲቀመጥ ተደርጓል። እንዲሁም ጉራማይሌ የሆነውን የኢንተርንሽፕ ቆይታ ጊዜን የተቀናጀ ርዝማኔ እንዲኖረው ተደርጓል።

የመመሪያው ክፍል ሶስት በአምስት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን ስለ የኢንተርንሽፕ አስተዳደር የሚደነግግ ነው። ይህም ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ሁሉንም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት እና የምርምር ተቋማት እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ትብብር ባረጋገጠ መልኩ የትስስር አካላት ለዚሁ ስራ ሀብት እንዲመድቡ እና ኢንተርንሽፕን የሚያስተባብር አደረጃጀት እንዲኖረው ተደርጓል። እንዲሁም የኢንተርንሽፕ ምዘና ስርአት እና ድጋፍና ክትትል አግባብ በበይነ-መረብ የታገዘ እና ተከታታይነት ያለው ሁሉም ተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በየዘርፋቸው ኢንተርኖችን እንዲመዝኑና ክፍተታቸውን በመለየት የሚደግፉበትን ስርአት ይደነግጋል።

የመመሪያው ክፍል አራት በአራት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን ስለ የፈፃሚ አካላት ተግባርና ሃላፊነትን ደንግጓል፡፡ ይህም ኢንተርንሽፕ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የባለዘርፈ-ብዙ ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ ተሳትፎን የሚፈልግ በመሆኑ ለባለድርሻ አካላት ግልጽ የሆነ ተግባርና ኃላፊነት ደንግጓል፡፡

የመመሪያው ክፍል አምስት በአራት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን ስለ መመሪያውን የማስፈጸም ኃላፊነት፣ መመሪያውን ስለማሻሻል፣ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ፣ የትስስር አካላት ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም እንደተቋማቸው ነባራዊ ሁኔታ የውስጥ መመሪያ እንዲያወጡ መብት እና ኃላፊነት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ በፊት በተለያዩ ስያሜ ይጠራ የነበረ የህግ፣ የጤና እና ሌሎች የተማሪዎች ወይም የሰልጣኞች የተግባር ስልጠና በዚህ የኢንተርንሽፕ መመሪያ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን ለተማሪዎች የተግባር ስልጠና ስያሜ የሚያገለግለውን "ኢንተርንሽፕ" በትስስር አዋጅ 1298/2015 እና በዚህ ረቂቅ መመሪያ ኢንተርንሽፕ የወል ስያሜ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 5. ህጉን ለማርቀቅ መነሻ የሆነ ፖሊሲ እና አዋጅ ስለመኖሩ፤

ረቂቅ መመሪያው ከአገሪቱ ህጎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ከትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እና  የሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ጋር መናበብ እንዲኖር እና ሌሎች ተዛማጅ የህግ ማእቀፎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የትስስር ስራ ተግዳሮት ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደመነሻ ተወስዷል፡፡